# የአንድነት ፓርቲ፤ የግሉ ፕሬስና የደደቢት በረሐ ውሾች ያስማሯቸው የአዳማ ቡችሎች

በአህመድ አባጊሣ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በሰላማዊ መንገድ ፈቃድ አውጥቶ የአገሪቱን ሕገመንግሥት አክብሮ ሕዝብን በተለየ የለውጥ ፖሊሲ የሚያታግል፤ ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ መዳበርም ከፍተኛ አስተዋፆ ለማበርከት ደፋ ቀና እያለ የሚገኝ ከአገሪቱ ትላልቅ ተቃዋሚዎች ተርታ የሚመደብ ፓርቲ ነው። አንድነት ገዢው ኢህአዴግ በውንብድና እና ዘረኛ አስተሳሰብ የሚመሩ፤ ለሰብዓዊ ፍጡር ከበሬታና ፍቅርን የማያውቁ፤ እስከጠቀማቸው ድረስ ባገኙት ላይ ሁሉ በመርዝ የተለወሰውን ውሃቸውን ከመርጨት ወደኋላ በማይሉ ጥቂት አብዮታዊ ዴሞክራቶች ቢመራም በጥላቻና በሃይል ግን ልንዋጋው አይገባም፤ ለዚህም የቱንም ያህል የማያፈናፍን ቢሆንም ባለው ሕጋዊና ሰላማዊ ክፍተት ሁሉ በመጠቀም ለውጥ ለማምጣት መታገል ይኖርብናል የሚለውን አቋሙን እስከመጨረሻው ይዞ ይቀጥላል። እንደ አንድነት ፓርቲ እምነት ኢህአዴግ ምንም እንኳ ከላይ እና በዋና ዋና እና ቁልፍ ቦታዎች ላይ አጥፍቶ ጠፊ ወንበዴዎችና በሙስና ተጨመላልቀው መድረሻ የጠፋቸው የእናት ጡት ነካሾች ቢመራም በአባላት፤ በመንግስታዊ መዋቅር እና በተለያዩ በኀብረተሰቡ ዘንድ በዘለቁ ሴሎቹ አማካይነት ጥሩ፤ መልካም ስብዕናን የተላበሱ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጆሯቸውን ቢቆርጧቸው የማይገባቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ በምርጫ 97 ከተቃዋሚ ወገን ቆመው ስለነበረ አሁን እንጀራቸውን ለማብሰል እና ራሳቸውንም ለማዳን ሲሉ በተሸጎጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሞላ በመሆኑ በጥላቻ ልንዋጋውና በሰይፍ ልንቀላው አይገባም ብሎ ያምናል።

ፓርቲው በተለያዩ መዋቅሮቹ አማካይነት ወደ ሕዝቡ በመዝለቅ በመንግስት ስለሚፈጸሙ የፖለቲካ ውንብድናዎች፤ አፈናዎች፤ የመልካም አስተዳደር በደሎች፤ የሕገ መንግስት ጥሰቶችና የፍትህ ስርዓት መጓደሎች በማውሳት ኢህአዴግን ፍፁም መሰረት ማሳጣትን ዓላማው አድርጎ የተነሳ ነው። ለገዢው ፓርቲ የሚከድሩት ከ 90% በላይ የሚሆኑት አባላት በቂ ዕውቀትና ችሎታ የሌላቸው፤ ታማኝነታቸውም ሆዳቸው ላይ ያለ፤ የአገርን ሀብት

የሚቦጠቡጡ፤ የሚናገሩትን እንኳ በውል የማያውቁ ብኩኖች መሆናቸውን ላለፉት 8 ወራት በበቂ ሁኔታ ባገኘው አጋጣሚ ሲያረጋግጥ ከርሟል፡፡ አሁንም አዳሜ ሲንጫጫና ሲንጨረጨር፤ ጠብመንጃ አንስቶ ሲፎክር ውሎ ቢያድር አንድነት እንደሆነ ከዚህ የተቀደሰ ዓላማው ስንዝር ያህል ፍንክች አይልም!

የአንድነት ፓርቲ ባሁን ወቅት ለ ምርጫ 2002 አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ፤ ያሉትና የቀሩት ጥቂት ነገሮችም ደብዛቸው እንዲጠፉ እነ አቶ እንደልቡና ጥቂት ደደብ ጀሌዎቻቸው የሚፈጽሙት ደባ እያለ ጥቂት የግሉ ፕሬስ አባላትና አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች እንደሚሉት ማውራት ያልተሳካና ያልሰመረ ጅምር ያለውን ትዳር ትቶ ስለ ሠርግ እንደማውራት ስለሚቆጥረው ለሚያወሩትም ያዝናል፡፡ የአንድነት ፓርቲ ስለ ምርጫው ከመወሳቱና ማን የት እንደሚወዳደር ከመወሰኑ፤ ዕጩዎችን ከማቅረብና ክልሎችን ከመወሰን፤ ሌሎች ዝግጅቶችንም ከማድረግ፤ በምርጫው እሳተፋለሁ፤ አልሳተፍም ከሚለውም በፊት መደረግ የሚገባው የፖለቲካ ስነ-ምህዳሩን ትርጉም ባለው መልኩ አሳታፊ እንዲሆን መጣር መሆኑን ያምናል፡፡ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅበትም ሕዝብን አደራጅቶ ለዚህ ለውጥ መነሳት እንጂ አንዳንድ መርቅነው የፖለቲካ ሜሞ እንደሚጽፉ ማፈሪያዎች እምቡር ብሎ እየተነሱ ስለ ምርጫ 2002 ማውራት አይደለም፡፡ አንድነት አሁን ያለው ሁኔታ እንዲሻሻል ምናልባትም ከሌሎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተሻለ እየተቀሣቀሠ ይገኛል፤ በዚህም ይቀጥላል፡፡ ይህ ባይሆን እና የአፓርታይድን ባሕሪ የተላበሰው ወታደራዊ ጁንታ አሻፈረኝ ካለ ግን በፖለቲካ ሜሞ፤ በርዕሰ አንቀጽ፤ በፊቸርና በተስፍሽና ገብርሽ መለቅለቅ ብልጠት የሚመስላቸው ቂሎች ይወርፉኛል ብሎ የኢህአዴግን ምርጫ እንደነ ኢዴፓ በአዳማቂነት አልያም እንደነ እነ አቶ አየለ ጫሚሶ ቅንጅት ደግሞ በአጃቢነት እንደማይባበት ያረጋግጣል፡፡

በዚህ መርህ የሚመራው አንድነት የግሉ ፕሬስ አባላት እንደሚቀባዥሩት ተበጣጥሶ፤ ተከፋፍሎ እርስ  በርሱም ተጠፋፎቶ የሚኖር ሳይሆን አሁንም የፓርቲው መላው አባላት ባመኑበት መልኩ ምንም እንኳ ቀደም ሲል ልዩነቶች ቢከሰቱም የፓርቲውን ስራ ከመስራት አልቦዘነም፡፡ የግሉ ፕሬስ በዶ/ር ኃይሉ አርአያና በፕ/ር መስፍን ወልደማርያም መሀከል ያለው እንካ ሰላንትያ ቢያጓጓውም አንድነት ግን እንደ ፕሬሱ ማበድ ስለሌለበት እነሱን ትቶ የፓርቲ ስራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከተያዙት ሕዝብን የማንቃትና የማደራጀት እቅዶች መሀከል አንዱ

የሆነውን በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ ሕዝብን የማወያየት ስራ ለማከናወን ባለፈው እሁድ ነሐሴ 10፤ 2001 ዓ.ም. ተጋባዥ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና የፓርቲው አመራሮች በዚህች ውብ ከተማ ተገኙ።

በዚህ ስብሰባ ላይ አንድነት በዋናነት አቅዶት የነበረውና ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችል የነበረው የአዳማ ከተማ ነዋሪዎችን የፖለቲካ ስነ-ምህዳሩ ላይ እየተፈጸመ የሚገኘው የማጥበብ ማንአለብኝነት ስራና የመንግስት ባለስልጣናት መባለግ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ጠንቅ መሆኑን ማሳየት ነበረ። ቆርጦና ታጥቆ የተነሣው አንድነትም ለዚህ ይረዳው ዘንድ ከከተማዋ መስተዳድር አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ነበረ። ወረቀቶችን በመበተን እና በመኪና ላይ ቅስቀሳ በማድረግ ሕዝብን ስለስብሰቧው አሳውቋል ጠርቷል። ዋናው የግብግብ ሜዳ ላይ ሲገባ ግን በፍሬ ነገሩ ላይ ተከራክሮ ነጥብን ከማስጣል ይልቅ ነጥብም ስለሌላቸው ጠለፋ፤  አስገድዶ መድፈርና፤ ጭቃ ቀብቶ መደብደብ የሚቀናቸው የደደቢት በረሐ ወንበዴዎች ከዛሬ 18 ዓመት በፊት ጀምሮ በተካኑበት በዚህ አስነዋሪ ድርጊታቸው ስብሰባውን ለመግታት ተንቀሳቀሱ። ‹የአካሄድ ጥያቄ!› በማለት አካሄዳቸው ወልጋዳ መሆኑ ሲነገራቸው የሚገባ ቅጥረኛ የ ኦህዴድ ጋኔን ወሮበሎች ምንም ባልገባቸው ነገር ስብሰባው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን በኦሮምፋ ቋንቋ መደረግ ይገባዋል ሲሉ የታዘዙትን እና በቃል ያጠኑትን ተቃውሞ አሰሙ።

እርግጥ ነው አዳማ ከምርጫ 97 በፊት የኦሮሚያ ዋና መዲና ነበረች። የኦሮሞን ባሕልም በሚገባ የምታንፀባርቅና የክልሉ እምብርት መሆኗም የማይካድ ነው። የአንድነት ፓርቲ የኦሮምፋ ቋንቋ በሃይል እና ሕዝብን በመግደል፤ በተለያዩ የነባራዊ ሁኔታዎች አመቺነትም ጭምር ከተስፋፋው አማርኛ ቀጥሎ ብሔራዊ ቋንቋ ለመሆን የሚችል ሰፊ ተናጋሪ ያለው የአገራችን የሕዝብ መግባቢያ መሆኑን ያምናል። በተለይም የክልሉን ሕዝብ ባህል፤ ወግ እና አኗኗር ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንቅስቃሴውን ማድረግ እንዳለበትም አይዘነጋም። ኦህዴድ ያሰማራቸው ወሮበሎች አንድነት የሕዝቡን ማንነት ሊዳፈር ነው ሲሉ ቆም ብለው ማሰብ የነበረባቸው የቅስቀሳ ወረቀቶቹን በኦሮምፋ ማሰራጨቱን ነበረ። ‹ነፍጠኛ›፤ ‹የአማራ ትምክህተኛ፤› ፤‹በብሔር ብሔረሰቦች መብት የማያምን፤› ወዘተ. ቢሆን ለምን ይህንን ያደርጋል? አይፀየፈውም ነበረ እንዴ እነ ቂሎ? ለነገሩ ኦህዴድና ኦሮሞዎቹ ሁሌም

አጎንብሰውና አፈንድደው ሕወሓት የሚዘራውን ከመልቀምና ከመላስ ሌላ ምን አምርተው ያውቃሉ? *Bilisuumaa* ን እና *Qiituumaaa* ን እንኳ ሕወሓት እኮ ነው ፈብርኮ ያስተማራቸው፡፡ የአንድነት ፓርቲ ለስብሰባው በአደራጅነት ካሰማራቸው አባላቱ አንድ የአማራ ብሔር ተወላጅ እንደሌለ አሥር ብቻ ጣት ስላለኝ በአስሩም አረጋግጣለሁ፡፡ ደደቦቹ የኦህዴድ ዘረኛ ኦሮሞዎች ግን ፊት ለፊታቸው ያለውን ሳይሆን ተቆጥሮ የሚሰጣቸውን እና በሴት እህቶቻችን ላይ በሚፈጽሙት አጸያፊ ወሲብ ወዲያውኑ የሚረጩትን የአረንጓዴ ኖቶች ረብጣ አይተው ነው የቋመጡት፡፡ የአንድነት ፓርቲ ዘረኛ እና ጠባብ ቢሆን አዳማ ላይ መርገጥን በተፀየፈ ነበረ፡፡ ክልላዊ አደረጃጀት ይዞ ብዙዎች የሚሄዱትን የማያዋጣ፤ ከግዜ በኋላም ቅሽምናው የተረጋገጠውን መንገድ በተከተለ ነበረ፡፡ ግን እነ ደደቦቹ ቶሎሣ እና ቂጤሳ እነ ወይንሸትና አሰፋ በቃና ሺህ ግዜ ይክፋቸው እንጂ አንድነት በኦሮሚያም ይንቀሳቀሳል፡፡ የአንድነት ፓርቲ ዘረኛ ቢሆን ኖሮ አዳማ የሚለውን ቃልም አልጠቀምም ባለ ነበረ፡፡ ያሰራጫቸው በራሪ ወረተቶች ላይ ናዝሬት የሚል ቃል እስካለመጠቀም የደረሠው በዘረኝነት ሳይሆን ለኦፊሴላዊ አጠራርና በሕግ ለተደነገገ፤ ሕዝብም ላመነበት የከተማዋ የቀድሞውና ኦሪጅናሌው ስም አውቅና በመስጠቱ ነው፡፡

ከሁሉም የሚያሳዝነው ጭንቅላታቸው አንጎልፋቶ የሆኑት እነ ቶሎሣና ዓለሙ ቂጤሳ ‹ስብሰባው በሕዝቡ ባሕል መሠረት በአገር ሽማግሌዎች ምርቃት መጀመር አለበት!› ማለታቸው ነበረ፡፡ አዎን እርግጥ ነው የኦሮሞ ሕዝብ የበርካታ ድንቃ ድንቅና አኩሪ ባሕሎች፤ ወጎችና ትውፊቶች ባለቤት ነው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ በነዚህ ከዘመን ዘመን ተሻግረው ኢትዮጵያን አልፈው በውጭው ዓለም እንኳ የሚልዮኖችን ቀልብ የገዙትን እሴቶች እና መገለጫዎቻቸውን በመያዙ ዝንተ ዓለም ይኮራል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ባሕሉን እና ወጉን ማንም እንዲያጎድፍብም ሆነ እንዲያራክስበት አይፈልግም፡፡ ነገር ግን በውቧና ታሪካዊዋ አዳማ ስንቱ የኦህዴድ ስብሰባ ነው በሽማግሌዎች ምርቃት የሚጀመረው? የቀድሞው ቅንጅት በአዳማ ካሸነፈ በኋላ በተለይም የንግዱን ማኅበረሰብ ከሰኔ 1997 ጀምሮ በመሰብሰብ ተላላኪዎቹ ኦህዴዶች ለማስፈራራት እና ለማሸማቀቅ፤ ‹ድምፃችሁን ለነፍጠኛ ሰጣችሁ! ከፈለግን ሰርታችሁ እንዳትበሉ እናደርጋችኋለን!› እና ሌላም እዚህ ለመጥቀስ የሚከብዱ የሚቀፉ ነገሮችን ሲናገሩ በሽማግሌ አስመርቀው ነው እንዴ? አይደለም! ትዝም አላላቸው፡፡ ምነው OPDO? ስንተዋወቅ አንተናነቅ ነው የሚባለው? የቀረፃችሁት ቪዲዮ እኮ እኛ እጅም ይገኛል፡፡ የአንድነት ፓርቲ የሚጨነቀው

ስለ ስብሰባ ፎርማሊቲ አልነበረም። ብዙ በአዳማም ሆነ በሌሎች የኦሮሚያ አካባቢዎች የሚካሄዱ ስብሰባዎች ይህንን እንደማያደርጉ እየታወቀ ይህንን መደቀን አጀንዳውን ደደቡ ኦህዴድ ወደፈለገው በዚያውም የደደቢት በረሐዎቹ ተናካሽ ውሾች ወደሚፈልጉት ለማድረግ የተቃጣ ካልሆነ ያን ያህል አሳሳቢ አልነበረም። አሁን ይኼ ነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳሳቢው? የተማረኩት ደደብ የደርግ/ኢሠፓ ወታደሮች ኦህዴድን ይዘው እንደ ድል አጥቢያ አርበኛ የታገሉት አልያም ሌሎች ደግሞ ከኦነግ ጋራ ዓመታትን ያጠፉት ለዚህ ነው እንዴ? የሽማግሌ ምርቃት ነው የሕዝብ አለኝታ? በርግጥ አንዳንድ ሃቀኛ አደራጆቻችን በቦታው ላይ ትክክለኛውን መልስ በመናገራቸው ይደነቃሉ። ሊመሰገኑም ይገባቸዋል። አንድነት በውስጡ በርካታ የኦሮሞ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን የያዘ በመሆኑ የኦሮሞ ሕዝብ ባሕልን እጅግ ያከብራል። ነገር ግን አሁን ዋናው አጀንዳ ዴሞክራሲው እና መልካም አስተዳደሩ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ በቋንቋው መናገር፤ ባሕሉን ማሳደግ ላለፉት 18 ዓመታት የቻለው ነገር ነው። ግን በቋንቋው የሕወሓት ማፊያ መሪዎች የፈለጉትን ካልሆነ ሌላ እናገራለሁ ቢል መቀመቅ እንዲወርድ ተወስኖበታል። ትግሉም ይህንን የአፓርታይድ-መሰል አፈና እናስቀር ነው። ባሕሉንማ ኢህአዴግም ቢሆን ኦሮሞዎቹ እስካጎነበሱለት ድረስ ያስጠብቅላቸዋል። ከስቅላት ልናድነው የሚገባው ዴሞክራሲያችንን እንጂ ኦህዴድም ለራሱ ሲል የሚያከብረውን ባሕል አይደለም።

ስብሰባው በምን ቋንቋ ይደረግ በምን ያን ያህል ማጨቃጨቅ ባልተገባው ነበረ። ቁም ነገሩ እሳት ላይ የቆመው ዴሞክራሲያችን እንጂ በውብ አማርኛ ወይንም ማራኪ ቅላፄ ባለው ኦሮምፋ መናገሩ አልነበረም። ግን ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም እንዲሉ አንዳንድ ኦህዴድ የላካቸው ጀሌዎች ድድብናውና ድንቁርናው ሰማያዊ ደማቅ ቀለም ካለው ዘረኝነታቸው ጋራ ተዳምሮ ራሳቸው ላይ ሊወጣ ደርሷል። በስብሰባው ላይ የበጠበጡት አልባሌ የኦህዴድ ተላላኪዎች ስድስት ሜትር ያህል አርቃ ማየት እንደማትችለው አህያ ሆነው ዋሉ። ለዚያውም ደደብ አህዮች!

ይህ አይነቱ በዴሞክራሲና በመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ላይ የተቃጣ አደጋ ዋናው አላማው ሁለት ነው። በቅድሚያ የተፈለገው ሕወሓት እንደ ጦር የሚፈራውና ባንደኛ ተቃዋሚነት የሚፈርጀው አንድነት ወደ ሕዝቡ እንዳይሰርጽ ማድረግ ነው። ሕወሓት ከ 18 ዓመታት የዳበረ ልምዱ በመነሳት እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስትን ስልጣን ዕድሉ ቢኖረው እንኳ

መውሰድ የሚችለው በሕብረ ብሔራዊ አደረጃጀት የተዋቀረው፤ የትኛውም ክልል ገብቶ ለመስራት የዘረኝነት፤ የጠባብነት እና የትምክህተኝነት አጥር የማይበግረው፤ በፖሊሲና በፕሮግራሙም ግልጽ እና ቀጥታ አማራጭን ለሕዝብ ማቅረብ የቻለው፤ በዲያስፖራውም ጭምር ተከታዮችን ማፍራት የቻለና የዓለም ዓቀፉን ማኅበረሰብና የዲፕሎማቶች ይሁኝታ ያገኘ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከአንድነት በላይ ራሱ ሕወሓትም ማንንም እንደ ምሳሌ አይጠቅስም፡፡ አዎን ጥቂት ሌሎች ተቃዋሚዎች አሉ፡፡ ጠንካራ ናቸው፡፡ ግን የሕዝብ ድጋፋቸው በሚንቀሳቀሱበት አንድና ሁለት ክልል አይደለም ጭራሽ ወደ ዞን እና ወረዳ ደረጃ የወረደ፤ የአንዳንዶቹም ከበርካታ ቀበሌዎች አልፎ የወረዳ ድጋፍ እንኳ ማግኘት ያልቻለ ነው፡፡ ስለዚህ ባንደበቱ ስለ ብሔር-ተኮር ፌዴራሊዝም ይልፍፍ እንጂ ሕብረ ብሔራዊውን ሁሉን-አቀፍ ኢትዮጵያዊነት እንደ ጦር ነው የሚፈራው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከሶስት ያላነሱ ብሔራዊ የመድበለ-ፓርቲ-መሰል ምርጫዎችን በማድረግ ወደር የሌለው ሕወሓት በማንኛውም ምርጫ ቢሆን (ኦነግ ጠንካራ ከነበረበት ምርጫ 84 ሌላ ማለት ነው ግን ኦነግ በምርጫ 84 አልተሳተፈም፤ እግሬ አውጪኝ ብሏል) ብሔር-ተኮር የሆኑ ፓርቲዎች ለስልጣኑ ሲያሰጉት አላየም፡፡

ሁለተኛው የመሠሪዎቹ ሕወሓት መሪዎች ዋንኛ ዓላማም የአንድነትን ህዝባዊ መሠረት ከማጥበብ ጋራ ጎን ለጎን ከክልሎቻችን በቆዳ ስፋትም ሆነ በሕዝብ ብዛት ግንባር ቀደም በሆነችው ውቧ ኦሮሚያ እንዳይሰራ፤ ለመስራት ቢያስብም እንኳ ‹ሕዝቡ አይቀበለኝም› ብሎ እንዲያስብ ለማድረግ፤ የኦሮሞን ህዝብ ከሕብረ-ብሔራዊው ፓርቲና ከቆመለት የሊብራል ዴሞክራሲ ዓላማ ለመነጠል የታለመ ግን የማይሳካ ውጥን ነው፡፡ በሕወሓት ስሌት አንድነት ከዚህች ስብሰባ በኋላ ኦሮሚያን መርገጥ ይፈራል፡፡ ግን ይህ ፈጽሞ የማይመስል ነው፡፡ በበርካታ የምሥራቅ ሸዋ፤ ከፊል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ እና ኢሉባቦር ወረዳዎችና ቀበሌዎች ፓርቲው አሁንም እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ነባራዊ ሁኔታዎችና አቅሙ በፈቀደ መጠን ደግሞ እንደ ጅማ፤ አርሲ እና ባሌ ባሉት ዞኖች መሠረቱን ለማስፋት አቅዷል፡፡ በዚህ ስብሰባ የራሳቸውን ቆሻሻ ድራማ ሰርተው ከአንድነት የተጋረጠባቸውን የመርህና የሐሳብ ጥያቄ ለማምለጥ ባጭር እይታ ያቀዱት እብዶቹ ሕወሓቶች አንድ ያልገባቸው ነገር ቢኖር አንድነት የቆመለት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፤ መልካም አስተዳደር እና መድበለ-ፓርቲ ዘር፤ቀለም፤ ፆታ እና ሃይማኖት እንደማይለይ ነው፡፡ ስለዚህ ውሾቹ ከቤተመንግስት አዳማ ላይ ባሰማሯቸው

ቡችሎች አማካይነት ሲጮሁ ውለው ቢያድሩ፣ ቢቀውጡት እና ክራንቻቸውን ቢያሳዩም ኢትዮጵያችን እና ሕዝቧ ግን ለዚህ ቦታ አይሰጥም።

ከዚህ አርቀው ማሰብ ከማይችሉት፣ ከስህተታቸው መማር ተራራን የመግፋት ያህል እየከበዳቸው በዘመን ላይ ዘመን፣ በሽበት ላይ ሽበት በጮማ ላይ ጮማ እየጨመሩ ከመሄድ ባለፈ ለአእምሯቸው አንዳችም የመንፈስ ምግብ መመገብ የተሳናቸው የአዳማ እና የአራት ኪሎ ውሾችና ቡችሎች አገርን የካደ (treasonous) ድርጊት ባልተናነሰ የሚያሳዝነው ደግሞ እስስታዊ ባሕሪን የተላበሱት የአንዳንድ የግሉ ፕሬሶችና አብረዋቸው የሚያላዝኑት አክራሪ፣ ጽንፈኛ የዲያስፖራ አባላት ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የግሉ ፕሬስ ሕገ-መንግስቱን በሂደት ትርጉመ-ቢስ (nominal) እንደሚያደርጉና ሕወሓትም ሁሌ አድረጊ ፈጣሪ እንዲሆን በር የሚከፍቱለት አፋኝ ሕጎች እንዳይፀድቁ ከሚችለው በላይ ጮኋል፣ ታግሏል። አሁንም እየታገለ ይገኛል። ሆኖም አሁን ከፀደቁትና ፕሬስን ወደ አይምሬው ስቅላት እንደሚመሩ ከሚታመንላቸው የፀረ-ሽብርኝነት እና አፋኙ የፕሬስ ሕግ አንፃር በርካታ የፕሬሱ አባላትና ዋና አዘጋጆች የፍርሀት ፖለቲካን ማራመድን ተያይዘውታል። የጥላቻን ፖለቲካ በማስወገድና ሃላፊነት የሚሰማው ፕሬስ መፍጠር ስም በርካቶች ሕዝብን ለለውጥ ከማነሳሳት፣ የሚጠበቅባቸውን ብልሹ አሠራሮችን እና የፍትህ መጓደልን፣ ብሎም የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ማጋለጥ ስራ በ self-censorship እየሸሹ ይገኛሉ። በተለይም ከ 97% በላይ የሆኑትን የፓርላማና የክልል ም/ቤት መቀመጫዎች ድራማ የማያልቅበት የስልጣን ጥመኛው ሕወሓት ያለ ምንም ሐፍረት ብቻውን ከጥቂት አጃቢዎች ጋራ ሮጦ በድጋሚ በእጁ እንደሚያስገባ እያወቁ ስለ ምርጫ 2002 እና ከተቃዋሚዎች ስለሚጠበቁ ነገሮች ማውራት አለማቆማቸው ያሳፍራል። በዚህ አሳፋሪ (shameful) ድርጊታቸውም በፀረ-ሽብርተኝነት እና በአዲሱ የፕሬስ ሕግ ፈርተው ድንብርብራቸው ስለወጣ ለምርጫ 2002 አዲስ አይነት አቀራረብ ይዘው ተነስተዋል። በዚህ አዲሱ አቀራረባቸውም ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚባለው ዓይነት ነው ሐሳባቸውና ውጥናቸው።

አንደኛው ሕወሓት እስር ቤት እንዳይከታቸው በተቻለ መጠን በተመረጡ፣ የፈሪ፣ ታግሎ የማያታግል፣ ራሱን ከተጠያቂነት ለማውጣት ሲል ገዢውን ፓርቲ የማያስከፋ ነገር ላይ በማተኮር መዘገብ እና በሚጓጉለትና ጋዜጦቻቸውን ሊያሸጥላቸው እንደሚችል በሚገምቱት

ምርጫ 2002 ላይ ላለመዘጋት መጣር ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቀደም ሲል በምርጫ 97 ወቅት ጭር ሲል አልወድም የሚለውን የአክራሪ ዳያስፖራዎች ቆሻሻ ፖለቲካ አራምደው አንዳንዶቹ ራሳቸው ከቅንጅት መሪዎች ጋራ ታስረው ለቅንጅት መፍረስ ተጠያቂ እንደሚሆኑት ሁሉ ሌሎቹ ደግሞ ትረፉ ሲላቸው መሪዎቹን ፓርላማ እንዳይገቡ ሲገፋፉ፤ ‹አቶ ልደቱ ከስብሐት ነጋ ጋራ ታዩ!› እያሉ ሲፅፉና ሲለቀልቁ ከርመው 2 ዓመት ከተደበቁ በኋላ ስማቸውን ቀይረው ጨዋ መስለው መቅረብ ጀምረዋል። ሌሎች ደግሞ በነዚህ ሁለቱ መሀከል፤ ‹የጥላቻን ፖለቲካ እናስወግድ› በሚልና ምንም የተጨበጠ መረጃ በማይሰጥ ከመንግስታዊው *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ ያልተሻለ ዱልዱምና ዱሽ አቀራረብ ይዘው መጥተዋል። ስለዚህ ይህ ሁለተኛው ዓላማቸው ቀደም ሲል ያቦኩትን የአክራሪነት ጭቃ ጠጋግኖና ጠፍጥፎ ለማስተካከል በዚያውም ከጌታቸው ሕወሓት ጋራ ጠላት ሳይሆኑ ለመኖር ሲሉ ከስነ-ምህዳሩ መጥበብ፤ በተቃዋሚዎች ላይ የሚደርሰውን ወከባ ከመዘገብ ይልቅ፤ ‹ተቃዋሚዎች ደካማና የተከፋፈሉ ናቸው!›፤ ‹ስነ-ምህዳሩ ቢሰፋም የሚረባ ተቃዋሚ የለም› የሚለውን ቀድሞውንም በኢህአዴግ የምርጫ ስትራቴጂስቶች ሲለፈፍ የነበረውን አጉል ጭፍን አመለካከት (sweeping generalization) እያጎሉ ማውጣት፤ በዚያውም ቀደም ሲል ለተፈጠረው የተቃዋሚዎች ድክመት ግንባር ቀደም ተጠያቂ የሆነውን ፕሬሱንም ከተጠያቂነት ማውጣት ነው። አሁን እንደምናየው የአዳማው የኦህዴድ ውንብድና ከአንድነት ፓርቲ ክፍፍል በላይ የሚዘገብ አይሆንም። ለምን? ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፕሬስ ለዚህ ደንታ-ቢስ ስለሆነ ነው። ነገር ግን የሚዘግቡት አንዳንዶችም ቢሆኑ ሽፍጠኛ በሆነ እና በሚያስቀይም መንገድ እያቀረቡት መሆኑ ያሳዝናል።

በመሠረቱ የ *አውራምባ ታይምስ* ጋዜጣ የፕሬስን ስቅላት ለማዳን ተግቶ የሚሠራ መሆኑ ይታወቃል። ነፃ ሐሳብን፤ ነፃ ንግግርን እና የሐሳብን በነጻነት መግለጽ፤ የዜጎችን ደህንነትና ዋስትና ቅድሚያ እየሰጠ የሚጽፋቸው ርዕስ አንቀጾች አጃቢ የፊቸር ጽሁፍና ብዙ ጉራማይሌ ቃላት ያሉበት ‹ምርምር› ሳያስፈልገው ገዢውን ፓርቲ የሚያስደነብር፤ በርካታ አንባቢያንንም ሊያነቃቃ የሚችል ነው። የ *አውራምባ ታይምስ* ጋዜጣ በተለያዩ ግዜያት በሕዝብ ላይ በ ‹ማሚያ ምርጫ› ስም የሚፈጸሙ በደሎችን፤ የዴሞክራሲ ተቋማት ላይ እየተፈፀመ የሚገኘውን የማዳከም እርምጃ እና ጥቂት አውቆ አበድ ብልጣብልጦች በሶስተኛ አማራጭ ስም ኢህአዴግን እና ዋናውን ሰውዬ ለመጥቀም ሲሉ የሚፈጽሙትን ክህደት ከማንም ጋዜጣ በላይ ቅንጣት ታክል ሳይፈራ ዘግቧል፤ አጋልጧል። የ *አውራምባ ታይምስ* ጋዜጣ ስለ አገራችን ኢትዮጵያ አሳዛኝ እጣ ፈንታ እና የዴሞክራሲ መታፈን የሚያገባው ዲያስፖራውም ጭምር

መሆኑን ለማሳየት በአገር ውስጥ ሆነው ፈራ ተባ እያሉ፣ ሕወሓት የሚወዳቸውን የከአንገት በላይ ቃላት ከሚጠቀሙ ጽሁፎች ይልቅ ኑሯቸውን በዲያስፖራ ያደረጉ የተማሩ፣ በርካታ ልምድን ያዳበሩ፣ በዘረኞቹ መሪዎች ለስደት በተዳረጉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚፃፉ በሳል፣ ከረር ያሉ፣ ውስጥን ሰርስረው የሚገቡ ጽሁፎች እንደ ሌሎች ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ አውጥቷል። በዚህም ከዘረኞቹ ማፊያ መሪዎች በርካታ መከራዎችን ተቀብሏል፣ እየተቀበለም ይገኛል።

ሆኖም የ *አውራምባ ታይምስ* ጋዜጣ አዘጋጆች ባንድ ግዜ ሁለት ጌቶችን ለማገልገል ሲሉ የሚሠሩ አይነት በመሆናቸው ለሕዝብ ታማኝ መሆን አቅቷቸዋል። በተለይም ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መዳበር ጠንቅ የሆኑ አክራሪና ጽንፈኛ የተቃዋሚ ዳያስፖራዎችን አካሄድ ከማጋለጥ ይልቅ ጭራሽ የነሱ ፍርፋሪ ለቃሚ መሆናቸው የሚያስተዛዝብ ነው። በዚህ የተነሣም ቆምንላቸው የሚሏቸውን የዴሞክረሲ እና የነፃ ሐሳብ መርሆዎች ከአክራሪ የዲያስፖራ ዌብ ሳይት አዘጋጆችና በጠብመንጃ ኢህአዴግን እንጥላለን ከሚሉ ጥቂት የቀድመው ቅንጅት መሪዎች በሚሰጣቸው ቀጭን ትዕዛዝ ሲጥሏቸው ይታያሉ። የ *አውራምባ ታይምስ* ባልደረባ የሆነ ሪፖርተር በዚህች ጉደኛ የዕለተ ሰንበት በአዳማ ከተማ ድርጊቱን ለመዘገብ ተገኘ። በእውነቱ ይህ ከአንድ የግል ጋዜጣ የሚጠበቅ በጎ ተግባር ነው። በዕለቱ ተገኝቶ ያየውን ሲዘግብ ግን ጥቁር እና ነጭ አድርጎ ትንሽ ለያይቶ ለሁለቱ ጌቶቹ እንደሚስማማ አድርጎ አቀረበ። በአገር ውስጥ ላለውና በፖሊሳዊው አምባገነን አገዛዝ እየማቀቀ ለሚገኘው ምስኪኑ ሕዝብ የሕወሓት መሪዎችን በማያስከፋ መልኩ፣

‹አንድነት በአዳማ ያዘጋጀው ስብሰባ በአካባቢው ተወላጆች ተቃውሞ ተቋረጠ›

ሲል ዘገበ። በዚሁ ዜናው ላይም ቀደም ሲል እኔ እንደጠቀስኩት ‹የአካሄድ ጥያቄ!› በማለት ተቃውሞ ያነሱ ተሳታፊዎች በመጨረሻም ስብሰባው እንዲቋረጥ ሁከት መፍጠራቸውን አስነበበ። እንግዲህ እዚህ ጋ ቁልፉ ቃል፣ ‹የአካባቢው ተወላጆች› የሚለው ነው።

ግን ይኸው ሁለት ጌቶችን በምስጢራዊ መንገድ የሚያገለግል ሪፖርተር በውጭ ለሚገኘው www.ethiopianreview.com ለተሰኘ የፕሬዚዳንት ኢሣይያስ አፈወርቂ እና የግንቦት 7 ቀንደኛ

ደጋፊ ድረ-ገጽም በተላላኪነት ስለሚሠራ ለሱ ዓይነት አቀራረብ የሚመጥን ዜና ሠራ ርዕሱንም፤

“UDJ Meeting In Nazret Disrupted by Woyanne Goons”

የሚል ርዕስ ሰጠው፡፡ በዚህኛው ዜና ደግሞ እነዚያን ‹የአካባቢው ተወላጅ› ሲል ለአገር ውስጥ አንባቢያን ያቀረባቸውን ወሮበሎች ‹የኦህዴድ ቅጥረኞች› ሲል ሀቁን አፍረጥርጦ ተናግሯል፡፡

በሁለቱ አቀራረቦች መሀከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ለምስኪኑ የአገር ውስጥ አንባቢ የቀረበለት እና ሊረዳ የሚችለው ነገር ስብሰባውን የአካባቢው ተወላጆች ከባሕላቸው እና ከልምዳቸው ጋራ ስለማይሄድ ማንም ሳይላቸው እንደተቃወሙት ነው፡፡ ‹አንድነት ከከተማዋ አስተዳደር አስፈላጊው ፈቃድ ተሰጥቶታል› የሚለን ይህ ዜና የአካባቢው ተወላጆች ቢቃወሙት እንኳ ማንም አነሳስቷቸው ነው ለማለት ምንም ፍንጭ የማይሰጥ ነገር ነው ያቀረበው፡፡ በሌላ በኩል በውጭ ሆነው የ ‹ጭር ሲል አልወድም›ን ክፉ ፖለቲካ መዋጥና መሰልቀጥ ሥራቸው ለሆነው አንባቢያን የቀረበው ደግሞ የኢህአዴግ (በሱና በኤልያስ ክፍሌ አጠራር ወያኔ) ጀሌዎች በአዳማ ሕዝባዊ ስብሰባን በተልዕኮ ማቋረጣቸውን ነው የሚነግረን፡፡

ሌላው ልዩነት ደግሞ ለአገር ውስጡ አንባቢ በግለጽ ያልተቀመጠ ለውጭው አንባቢ ግን እንዲገባውና ግንዛቤ እንዲይዝም በአጽንኦት ጭምር የተቀመጠ ነገር መኖሩ ነው፡፡ በኢትዮፒያንሪቪው ድረ-ገጽ ላይ የወጣው ዘገባ ውስጥ፤

> “The Woyane thugs and goons have even gone to the extent of physically assaulting former Ethiopian President, Dr. Negasso Gidada. They accused him of being used by the Neftegna Amharas. Interestingly, the Woyane goons didn’t lay a finger on EPRDF’s pointman in the newly formed FDD, Siye Abaraha. Siye could watch all this together with Dr. Beyene Petros. The goons left the hall after their fomer boss, Siye, went out unattacked.”

ይህ በአዳማ ካየነው የደደቦቹ ተላላኪ ቡችሎች ውንብድና የማይተናነስ በአቦ ሰጡኝና በአሽባሪነት መንፈስ የሚፃፍ የስሜት ፖለቲካን የሚያንፀባርቅ ወራዳ ስራ ነው፡፡ ኤሊያስ ክፍሌ የፐ/ት ኢሣይያስ ተላላኪ እንደመሆኑ መጠን እሳቸው የሚሉትን እንደ በቀቀን መደጋገም ይጠበቅበታል፡፡ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ግዜ የሻአቢያ ጦር መግቢያ መውጫ ጠፍቶት በፍርሀት እንዲርበደበድ ያደረገው በስዬ አብረሐ የተመራው የኢትዮጵያ ጦር ነበረ፡፡ የነ ስዬ የሕወሓት የትግራይ ክንፍ ሻአቢያን አስመራ ላይ ሄዶ እስከማውረድ የሚዘልቅ ቁርጠኝነትና ፍላጎት በማሳየቱ ፕሬዚዳንቱ በስዬ፤ ገብሩ፤ አረጋሽ እና ሌሎቹ የዚህ የቀድሞው ሕወሓት አንዱ አንጃ ላይ ቂም ቢይዙ ምንም አያስገርምም፡፡ ለዚህ ሲባልም፤

> ‹አምባገነኑ አቶ _________ ቅንጅትን የሚመስል ሌላ ማንም እንደሚያሸንፍ ቢያቁና አማራጭ ቢያጡ ስዬን ስልጣን ላይ በማውጣት የሕወሓትን የበላይነትን ለማስጠበቅ ነው የሚጥሩት›

ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ይኼ ምንም ማረጋገጫ የሌለው የሻአቢያና መሰሎቹ ፖለቲካ ነው፡፡ አንድነትን ‹የኦሮሞን መብት አላከበርክም› ወይንም ‹ነፍጠኛ ነህ› ብለው የሚከሱ ወርበሎችና ጠባብ ዘረኞች ለአንድነት የሁሉን አቀፍ ማረጋገጫ የሚሰጡ የሚመስሉትን ኦሮሞውን ዶ/ር ነጋሶን እንጂ ስዬን ለምን ይደበድባሉ? ዘረኛ የሆነ ሰው የራሱ ዘር የሆነ ሰው፤ ‹ተው እረፍ!› ቢለው ከዚህ ሰው በላይ ሌላ በማንም አይናደድም፡፡ እና እስከ አሁን እስርም ሆነ የአካላዊ ድብደባ ያልደረሰባቸውን እና ከብሔር ተኮሩ ፖለቲካ ሻል ያለ አቀራረብ እውቅና በመስጠት new paradigm እያመጡ ያሉትን ዶ/ር ነጋሶን በዚህ አጋጣሚ ይደበድባል እንጂ ኢህአዴግ አቶ ስዬን ለምን ይነካል? ነገር ግን ‹ስዬ ያልተመቱት አቶ ________ ከአሁኑ ለስልጣን እና ለቀጣዩ ጠ/ሚኒስትርነት ያጯቸው በመሆኑ ነው!› ብሎ ማግራት ድንቁርና ነው የሚሆነው፡፡ ስም ማጥፋት ነው የሚሆነው፡፡ አጉል ቧልትና ተራ የካቲካላ ቤት ወሬም ጭምር ነው የሚሆነው፡፡ ሻአቢያ የኢትዮጵያን ተቃዋሚዎች እንዲህ አድርጎ ለመከፋፈል ሲል ቢወጥን ምን ሊገርም? የሚገርመው ማሰቢያ የሌላቸው እስከሚመስሉ ተከትለውት በጭቃ የሚንቦጫረቁት እነ ኤሊያስ ክፍሌ እና እነ ፍፁም ማሞ ናቸው እንጂ!

ሌላውና በዚህ የኤሊያስ ክፍሌ ዜና ላይ አሳዛኙ ነገር ደግሞ ለሕዝብ የዘመናት ትግል እና ኦፌሴላዊ አጠራር እውቅና ላለመስጠት፤የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችንም ምንም እንደማይገባቸው ደደብ ተከታዮች አድርጎ ለማቅረብ የተወጠነው ሴራና አስቀያሚ አቀራረብ ነው። በዜናው መጀመሪያ ላይ፤

> "Woyanne goons disrupted a meeting last Sunday in Adama (the new name given to Nazret by Woyanne) organized by Ethiopia's main opposition, Unity for Democracy and Justice (UDJ)."

ይኼ ደግሞ ፈር የለቀቀና የሚቀፍ ውንጀላ ነው የሚሆነው። አዳማ እኮ የከተማዋ ስም እንጂ ኢህአዴግ (ወይንም በነሱ ወያኔ) የሰጣት ስም አይደለም። አዳማ ቀድሞውንም የከተማውና የአካባቢው መጠሪያ ሆኖ የቆየ ነገር ግን በቀድሞው ስርዓቶች ወደ ናዝሬት የተለወጠ ነው። ስለዚህ ለሕዝቡ ባሕላዊ ትውፊቶችና መጠሪያዎች እውቅና መስጠት ሲገባ እንዲህ ብሎ መፃፍ ከአንድ ለዴሞክራሲ ቆሜያለሁ ከሚል ጋዜጠኛ (ይቅርታ ጋዜጠኛ አልኩ እንዴ?) የማይጠበቅ ነው:: ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊነት ሙሉ እና ትርጉም ያለው ሊሆን የሚችለው የእያንዳንዱን የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰብ ፍላጎት ሲያንፀባርቅ እንጂ ‹እኔ አውቅልሀለሁ› የሚለውን የቀድሞን ስርዓት ጨቋኞች ቀረርቶ መልሶ ሲያሰማ አይደለም። የብሔር ጭቆና የነበረ መሆኑን አንድነትም ግንቦት 7ም ይቀበላሉ። ኤሊያስ ክፍሌ ግን በዚህ የለየለት ትምክህተኛ አስተሳሰቡ ተቃዋሚዎችን ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና የሕዝብ ፍላጎት ነጥሎ የሱ ተላላኪ ሊያደርጋቸው ይሞክራል። በዚህ እኩይ ድርጊትና ጽሁፍ ደግሞ ዋና አዘጋጁ ፍፁም ማሞ መጠየቅ እንዳለበት ቅንጣት ታህል አያጠራጥርም። የአቶ ስዩ አብርሐን ስም የሚያጎድፍና የአዳማን ከተማ ትክክለኛ መጠሪያ የሚያዛባ ነገር እየፃፉ መስጠት ትልቅ ውንብድና ነው።

ለማንኛውም ስብሰባውና የቀረበው አጀንዳ አንድነት ፓርቲ ወደኋላ ሳይሆን ወደፊት በመገስገስ በትግሉ የሚጠበቅበትን ለማድረግ ሳንካዎች እንደማይበግሩት ያሳየ ነው። ስብሰባውን ለማቋረጥ የተደረገው ጥረት ደግሞ ሕወሓት አንዳንድ የግሉ ፕሬስ አባላት በርዕሰ አንቀጾቻቸውና በፊቸሮቻቸው እንደሚቀባዥሩት ሳይሆን የሕብረ ብሔራዊ ፓርቲ ስኬት ስለሚያስጨንቀው

የብሔር ግጭት ቀስቅሶ ለማዳከም እንደሚጥር ነው። ኢህአዴግ አንዳንድ ወጣት የጋዜጣ አዘጋጆች እንደሚሉን ሕብረ ብሔሮችን ብዙም የማይፈራ ቢሆን እግሩን አዳማ ላይ ባላነሳ ነበረ። በሌላ በኩል ሕብረ ብሔራዊ የተባለን ሁሉ ደግሞ ከቁብ አይቆጥርም። ኢዴፓ በወላይታ እና በሃዲያ ሄዶ ሲንጫጫ ለምን ዝም አለ? ኢህአዴግ ለዱልዱሞች ስለማይጨነቅ ነው።

## አቶ አህመድ አባጊሣ የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከፍተኛ አደራጅ አባል ናቸው